# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 223822

ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ - ነ/ፈጅ ሳሙኤል ባዬ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ሄኖክ ፈሰፋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡ ተጠሪ መስከረም 14 ቀን 2012 ዓ/ም ጽፎ ያቀረበው ክስ ኦክስፎርድ አማልጋሜትድ ኃ/የተ/የግል ማሕበር የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ባለመሰብሰቡ ብር 33,213,016.57 ውዝፍ ዕዳ መክፈል አልቻለም፤ የድርጅቱን ንብረት በብድር ዕዳ ምክንያት የያዘው አመልካች ቅድሚያ ለተጠሪ እንዲከፍል ሲጠየቅ በፍርድ ቤት ታግዷል በማለቱ ፍርድ ቤት ቀርበን እግዱ እንዲነሳና በቀዳሚነት እንዲከፈለን የታዘዘ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቢሆንም አመልካች ምላሽ ያልሰጠን ስለሆነ በሰበር መዝገብ ቁጥር 122258 በተሰጠው ትርጉም መሠረት ብር 33,213,016.57 ከወለድ ጋር አመልካች እንዲከፈል እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ አመልካች ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 202884 ጉዳዩ ቀርቦ ትዕዛዝ የተሰጠበት ነው፤ ፍርድ ቤቱ አመልካች ከድርጅቱ የሚፈልገውን ዕዳ ቀንሶ ብር 23,479,362.17 ለተጠሪ እንድንፈጽም አዟል፤ ተጠሪ የባንክ ወለድና ቅጣት መጠን በመጨመር ያቀረበው ክስ በፍርድ ያለቀ ነው፣ የቀዳሚነት መብቱን ማስከበር እንጂ አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም፣ ጉዳዩም የሚቀርበው በሰ/መ/ቁ. 131084 እንደተወሰነው ለአፈጻጸም ችሎት ነው፤ ስህተት ካለም በይግባኝ ማሳረም እንጂ አዲስ ክስ ማቅረብ አይቻልም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪ ባቀረበው መልስ ቀደም ሲል በፍርድ ቤት ጣልቃገብተን እግድ ይነሳ በማለት ጠየቀን እንጂ በቀዳሚነት መብት ላይ ክርክር አላደረግንም፤ አመልካች የተጠሪን የቀዳሚነት መብት ተላልፎ ገንዘቡን ስለወሰደ እንዲመልስ የቀረበ ክስ መቅረቡ ተገቢ ነው ሲል አቅርቧል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 242001 ላይ ግራቀኙን አከራክሮ ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 202884 ተጠሪ አመልክቶ የቀዳሚነት መብት ስላለው የጠየቀው ብር 23,479,362.17 እንዲከፈለው ትዕዛዝ ተሰጥቷል፤ አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ ተከራካሪ ያልነበረ ቢሆንም ተመሳሳይ ጉዳይ በመሆኑ በፍርድ ያለቀ ነው፡፡ ተጠሪ በትዕዛዙ መሠረት ካልተፈጸመለት አፈጻጸም በማቅረብ መጠየቅ ከሚችል ውጭ በቀጥታ ክስ ማቅረቡ ምክንያታዊ አይደለም፡፡ ተጠሪ ክስ ካቀረበበት የገንዘብ መጠን ውስጥ ከብር 23,479,362.17 ውጭ ያለው ገንዘብ ብር 9,733,654.40 ሲሆን ገንዘቡ ወለድና ቅጣት በመጨመር የቀረበ በመሆኑ ቀድሞ ተጠሪ አጠቃሎ ክስ ሊያቀርብበት ይችል የነበረ ስለሆነ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(3) መሠረት ተቀንሶና ተነጥሎ የቀረበ ዳኝነት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ ተቀብሎ ያከራከረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተጠሪ ቀደም ሲል እግድ እንዲነሳ የጠየቀበትና አሁን በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ የተለያየ ጭብጥ፣ የተለያየ ተከራካሪ ያለው በመሆኑ ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ አይደለም፡፡ አመልካች ላይ ቀድሞ የተጠየቀ ዳኝነት ባለመኖሩም ተቀንሶ የቀረበ ነው የሚያስብል አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ በሥረ-ነገሩ ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩን መልሷል፡፡ ፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ መመልከቱ ተገቢ አይደለም፤ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 202884 ላይ የቀዳሚነት መብቱን ለማስከበር ክርክር ማቅረቡ ባልተካደበትና ቀድሞ ሆነ አሁን የሚያከራክረው የቀዳሚነት መብት ጉዳይ ስለሆነ ተመሳሳይ የሕግ ሆነ የፍሬ ነገር ጭብጥ ስለሆነ ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው፡፡ ተጠሪ የተሰጠው ትእዛዝ መብቱን የሚነካው ከሆነ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በይግባኝ ከማሳረም ውጭ አዲስ ክስ ሊያቀርብ አይችልም፡፡ ተጠሪ የፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ሳያወጣ ከሦስት ወራት በኋላ ቆይቶ ገንዘቡን ለመውሰድ በሚመጣበት ጊዜ ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ተከፍሏቸው ተጠናቋል፡፡ ጉዳዩም ተነጣጥሎና ተቀንሶ የቀረበ በመሆኑ የክስ አቀራቡ ሕግን የተከተለ አይደለም፤ ውሳኔው ሊሻር ይገባል የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ቀድም ሲል በመዝገብ ቁጥር 202884 ላይ እግድ እንዲነሳና ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ ሊከፈል እንደሚገባ ተጠይቆ በ09/04/2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ተሰጥቶ እያለ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀድሞ ያልቀረበ ጥያቄ እና ያልተከራከሩበት ነው በማለት የወሰነበት አግባብነትን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው መልስ ከኮሮና ወረሽን መከሰት ጋር ተያይዞ በወጣው መመሪያ መሠረት ይግባኙን በሕጉ አግባብ አቅርበናል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ሌሎች ተከራካሪዎች በነበሩበት መዝገብ እግድ እንዲነሳ መጠየቃችን ከአመልካች ጋር መከራከራችንን አያሳይም፡፡ አሁን ከቀረበው ክስ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጭብጥ የለውም፡፡ አመልካች የድርጅቱን ገንዘብ በቀዳሚነት ለተጠሪ መክፈል ሲገባው ለሌሎች ባለገንዘቦች አሳልፎ በመስጠቱ ምክንያት ክስ ማቅረባችን ተገቢ ነው፤ ውሳኔው ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር፣ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ መስከረም 14 ቀን 2012 ዓ/ም ጽፎ ያቀረበው ክስ ኦክስፎርድ አማልጋሜትድ ኃ/የተ/የግል ማሕበር የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ባለመሰብሰቡ ብር 33,213,016.57 ውዝፍ ዕዳ መክፈል አልቻለም፤ የድርጅቱን ንብረት በብድር ዕዳ ምክንያት የያዘው አመልካች ቅድሚያ ለተጠሪ እንዲከፍል ሲጠየቅ በፍርድ ቤት ታግዷል በማለቱ ፍርድ ቤት ቀርበን እግዱ እንዲነሳና በቀዳሚነት እንዲከፈለን የታዘዘ ቢሆንም አመልካች ምላሽ ያልሰጠን ስለሆነ በሰበር መዝገብ ቁጥር 122258 በተሰጠው ትርጉም መሠረት ብር 33,213,016.57 ከወለድ ጋር አመልካች እንዲከፈል እንዲወሰን የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 202884 ጉዳዩ ቀርቦ ትዕዛዝ የተሰጠበት ነው፤ ፍርድ ቤቱ አመልካች ከድርጅቱ የሚፈልገውን ዕዳ ቀንሶ ብር 23,479,362.17 ለተጠሪ እንድንፈጽም አዟል፤ ተጠሪ የባንክ ወለድና ቅጣት መጠን በመጨመር ያቀረበው ክስ በፍርድ ያለቀ ነው፣ የቀዳሚነት መብቱን ማስከበር እንጂ አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን

*ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት በሕግ ሥልጣን የተሠጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከሠጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ፤ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ማቅረብ አይችሉም፡፡ በድንጋጌው መሠረት ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት የተዘረዘሩት አራት መስፈርቶች በአንድነት መሟላት አለባቸው፡፡

የመጀመሪያው መስፈርት ጉዳዩን የተመለከተው <u>በሕግ ሥልጣን የተሠጠው</u> (ሠረዝ የተጨመረ) ማናቸውም ፍርድ ቤት መሆኑ ነው፡፡ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የሚለው አስቀድሞ ጉዳዩ የታዬው በሕግ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም ዳኝነት ነክ አካል መሆኑን ለማመላከት ነው፡፡ ሁለተኛው መስፈርት አስቀድሞ በፍርድ ቤት የተሠጠው የመጨረሻ ፍርድ መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን አይቶ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ እልባት ወይም ውጤት የሠጠበት መሆን እንዳለበት የሚያስረዳ መስፈርት ነው፡፡ ሦስተኛው መስፈርት አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ሥረ-ነገሩና ጭብጡ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ጉዳይ አንድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት የመረመረው ጉዳይ አሁን በተያዘው ክርክርም በጭብጥነት ተይዞ የሚመረመር ከሆነ ውጤቱ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ይሆናል፡፡ ሥረ-ነገሩ ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን የሚያዘው ወይም የተያዘው ጭብጥ የተለያዬ ከሆነ በተያዘው ጭብጥ ላይ የቀደመ ፍርድ ባለመኖሩ ጉዳዩ በፍርድ እንዳለቀ ሳይቆጠር ክርክሩ ቀጥሎ ፍርድ ሊያርፍበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ በሕጉ ላይ የተቀመጠው አራተኛው መስፈርት የተከራካሪዎች ወይም ከተከራካሪዎች መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች ተመሳሳይ መሆን እና በእነርሱ መካከል ያለ ክርክር መሆኑ ነው፡፡ የዚህ መስፈርት መነሻ ፍርድ የአስገዳጅነት ሀይል ሆነ ውጤት የሚኖረው በተከራካሪዎች መካከል ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ ከተከራካሪዎች ውጭ ፍርዱን በመያዝ መብት ማቋቋም ሆነ ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የሚመረምረው ሆነ ፍርድ የሚሠጠው ከተከራካሪዎች መካከል የተሻለ መብት ያለው ማን ነው ከሚለው ነጥብ አኳያ ብቻ ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ ያላቸው መብት በፍርድ ቤቱ ሳይመረመር እና የመደመጥ ሆነ የመከላከል መብታቸው ሳይከበር ተከራካሪ ያልሆኑ ወገኖች ላይ ፍርዱ አስገዳጅነት አለው ሊባል አይችልም፡፡ የተከራካሪዎች ተመሳሳይነት የሚለው ከተከራካሪዎች በሕግ ሆነ በውል መብት የተላለፈላቸውን ሦስተኛ ወገኖች የመብታቸው ምንጭ የቀድሞው ክርክር ላይ ተከራካሪ በሆኑት ወገኖች ልክ በመሆኑ በእነዚህ ወገኖች ላይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ነው፡፡

*ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት ከተመለከትን ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ኦክስፎርድ አማልጋሜትድ ኃ/የተ/የግል ማሕበር የተባለው ድርጅት ያልሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ላይ ለማስከፈል የድርጅቱ ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት እያለንና መብታችንም በፍርድ ቤት አስከብረን እያለ በአመልካች እጅ ከነበረው የድርጅቱ ገንዘብ ሊከፍለን ስላልቻለ አመልካች ብር 33,213,016.57 ከወለድ ጋር እንዲከፈል እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ይሕም ዕዳ የነበረበትን ድርጅት ንብረት አከፋፈል ላይ አመልካች ሰራ በተባለው ጥፋት ለገንዘቡ አመልካች ተጠያቂ ነው በሚል ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ተጠሪ ክስ ማቅረቡን ያሳያል፡፡ ተጠሪ አሁን ካቀረበው ክስ ውጭ አመልካች ላይ ሌላ ክስ ያቀረበ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር የለም፤ አመልካች የሚከራከረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 202884 አመልካች ከድርጅቱ የሚፈልገውን ዕዳ ቀንሶ ብር 23,479,362.17 ለተጠሪ እንድንፈጽም ትዕዛዝ ስለተሰጠ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ነው በማለት ነው፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 202884 ላይ ተጠሪ ክስ አላቀረበም፣ በአፈጻጸም ክርክር ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ጣልቃ ገብቶ ፍርድ የሚፈጽመበት ንብረት ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት ለማስከበር መከራከሩ ሆነ ትዕዛዝ መሰጠቱ አመልካች ላይ ክስ አቅርቦ እንደተወሰነ የሚወሰድ አይደለም፤ በአፈጻጸም መዝገብ የቀረበው ክርክር እና አሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት ያደረገ ክስ የተለያየ ማዕቀፍ ያለው በመሆኑ ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ተብሎ መቃወሚያ ሆነ ክርክር የሚቀርብበት አይደለም፤ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የአመልካችን መከራከሪያ ውደቅ ማድረጉ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ቀደም ሲል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 202884 ከቀረበው ክርክር ጋር ሲታይ ተነጣጥተሎ የቀረበ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(2 እና 3) መሠረት በአንድ የክስ ምክንያት ጋር በተያያዘ የሚጠየቅ ዳኝነት አንድ ጊዜ ተጠቃሎ መቅረብ እንዳለበትና ተነጣጥሎ ከቀረበ ክሱ ተቀባይነት እንደማይኖረው ተመልክቷል፡፡ ክሱ ተጠቃሎ የቀረበ ነው ወይስ ተነጣጥሎ የቀረበ ነው የሚለውን ከመመርመሩ በፊት ተጠሪ አሁን ካቀረበው ክስ በፊት አመልካች ላይ ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት አድርጎ ክስ ያቀረበ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአፈጻጸም ክርክር መብቱን ለማስከበር ያደረገውን ክርክር አመልካች ላይ ክስ እንዳቀረበ በመቁጠርና ከአፈጻጸም ክርክሩ ጋር በማነጻጸር ክሱ ተነጣጥሎ የቀረበ ነው በሚል መወሰኑ ሕጉን ያልተከተለ ነው፤ በዚህ ረገድ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ስሕተቱን በማረም ጉዳዩ በሥረ-ነገሩ ተመልክቶ እንዲወስን መመለሱ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

# ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 195708 ጥር 25 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

# ት ዕ ዛ ዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- በዚህ ችሎት መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም